# በፌዴራል የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት 7ኛ ዙር ቋሚ የጋራ ምክክር መድረክ ጉባኤ

## የተዘጋጀ ንግግር፣

- ክቡር አቶ ሰለሞን አፈወርቅ፡- የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ፕሬዝደንት፤
- የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የሥራ ኃላፊዎች፣
- የክልልና ከተማ አስተዳደሮች፣ የገ/ኢ/ል/ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች፣
- የፌዴራል መንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የሥራ ሃላፊዎች፣
- የፌዴራል መንግሥት የግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የሥራ ሃላፊዎች፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች፣
- የልማት አጋሮቻችን እና
- የመገናኛ ብዙሃን ተወካዮች፣
- ጥሪ የተደረገላችሁ ዕንግዶች፣

ክቡራትና ክቡራን፣

የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመንግሥት ትልቅ ትኩረት በተሰጠው ከንግዱ ህብረተሰብ እና ከልማት አጋሮቻችን ጋር ለ7ኛ ዙር ቋሚ የጋራ ምክር መድረክ ላይ ተገኝቼ የመዝጊያ ንግግር ሳደርግ የተሰማኝን ደስታ በራሴና በፌደራል የመንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ስም ለመገለጽ እወዳለሁ፡፡

መንግሥት የአጭር፣የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ የልማት ዕቅዶችን ነድፎ ለተግባራዊነቱ መላውን የሀገሪቱን ህዝቦች በማስተባበር ባለፉት ዓመታት በርካታ የልማት ሥራዎችን በማከናወን በዓለም ፈጣን ዕድገት አላቸው ከሚባሉ አገሮች በቀዳሚነት ተጠቃሽ እንድትሆን አድርጓታል፡፡ በዚህም የተነሳ በአገራችን በመካሄድ ላይ ያለው መጠነ ሰፊና ፈጣን እድገት ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ እንዲሆን የማድረግ ግብ ተይዞ በመሰራቱ፣ብዙ ሀብታሞች የሚፈጠሩባት አገር ብቻ ሳትሆን ዜጎች በየደረጃው ከዝቅተኛ ወደ መካለኛ ገቢ በፍጥነት መሸጋገር የጀመሩባት አገርም ሆናለች ፡፡

በአገራችን የተዘረጋውን የነፃ ገበያ ስርዓት ኢኮኖሚው ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር እንዲራመድ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠሩ ከጥቃቅንና አነስተኛ እስከ ከፍተኛ እንዱስትሪዎች

እንደአሸን እንዲፈሉ አድርጓል፡፡ ከትናንሽ እስከ ሜጋ የመሰረተ ልማቶችንና ፕሮጀክቶችን ነድፎ ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ከታላቁ የህዳሴ ግድብ እስከ ባቡርና ሰፋፊ አውራ ጎዳናዎች፣ ከገጠር ኤሌክትሪፍኬሽን እስከ ሰፊ የቴሌኮም አውታር ዝርጋታ ድረስ የሚደረገው እንቅስቃሴ በእውነትም ከድህነት ጋር የገጠምነውን ጦርነት በአሸናፊነት እየተወጣን መሆኑ ግልፅ ነው ፡፡

*መንግሥት ለሚያንቀሳቅሳቸው ዘርፈ ብዙ የመሠረተ ልማት ሥራዎች ማስፈፀሚያ የሚያስፈልገውን ገንዘብ የሚያገኘው በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ከተሠማሩ ዜጐችና ኩባንያዎች በግብርና በቀረጥ መልክ በሚሰበሰበው ገንዘብ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥም ትልቁን ድርሻ የሚይዙት የንግዱ ህብረተሰብ በማለት የምንጠራው አምራቹ፣ አከፋፋዩ፣ በግንባታ ዘርፍ ሥራ የተሰማራው፣ የምክር አገልግሎት እና ሌሎች በፋይናንስ እና በሆቴል አገልግሎት … ወዘተ ዘርፎች የተሠማሩ አካላትና ዜጐች እንደሆኑ ይታወቃል፡፡*

*በግብር መልክ በተገኘው ገንዘብ መንግሥት ሰፋፊ የመሠረተ ልማት ሥራዎችን ለማከናወን እና ሌሎች አገራዊ ጉዳዮችን ለማስፈፀም ግልፅ፣ ከአድልኦ የፀዳና ተጠያቂነት የሰፈነበት የመንግሥት የግዥ ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ አብዛኛው የግንባታ ሥራ፣ የምክር አገልግሎት፣የዕቃዎች እና ሌሎች አገልግሎቶች ግዥዎች ለሙስና እና ለኪራይ ሰብሳቢነት የተጋለጡ በመሆናቸው ሁለቱም ተወናይ ወገኖች ማለትም ግዥ ፈጻሚውና የንግዱ ህብረተሰብ የጋራ አጀንዳ ቀርፀው በዘርፉ በሚያጋጥሙ ችግሮችና የመፍትሔ አቅጣጫዎች ላይ በጋራ ለመወሰን 6 መደበኛ የጋራ ምክክር መድረኮችን አካሂደናል፡፡ በተለይም ከጨርቃጨርቅና አልባሳት አምራቾችማህበር፣ከኮንስትራክሽን ዘርፍ፣ከብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሚነሱ ጥያቄዎች ሁለንተናዊ ጥቅም የሚያስገኙ መሆናቸው በመንግስት በኩል ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡*

**ክቡራትና ክቡራን**

*የመንግሥት ሀብት በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ላይ ያተኮሩ የተለያዩ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ማሻሻያ ሥራዎችን ሲያከናውን በመቆየቱ የአገር ውስጥ አቅራቢዎችን በመደገፍ ላይ የገኛል ለወደፊትም ድጋፉ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡*

*ይህ የጋራ ምክክር መድረክ የመንግሥትን የግዥ ስርዓት እና አሠራሩን ማንኛውም ወገን በግልጽ መረዳት እንዲችልና አድሎአዊ አሠራርን በመከላከል የልማታችን ፀር የሆነውን ሙስና እና ኪራይ ሰብሳቢነትን ለመታገል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው ከመሆኑም በላይ በብረታብረትና ኢንጂነሪንግ እንዱስትሪዎች፣ በጨርቃጨርቅና አልባሳት አምራቾች የሚስተዋለውን የገበያ ችግር ለመቅረፍና የገበያ ትስስር ለመፍጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡*

በመጨረሻም እንደዚህ አይነት መድረኮች ከመንግሥት ግዥ ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሙ የአፈጻጸም ችግሮችን ለመፍታት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑ ስለሚታመን መድረኩ ለወደፊት የበለጠ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የመንግሥት ፍላጐት መሆኑን እየገለፅኩኝ፤ የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት እና ሌሎች የንግዱ ባህበረሰብ ለዚህ የጋራ ምክክር መድረክ መሳካት ላደረገው አስተዋጽኦ በራሴና በኤጀንሲው ስም አያመሰገንኩ ይህ 7ኛው ዙር የጋራ ምክክር መድረክ ጉባኤ በይፋ የተዘጋ መሆኑን እገልጻለሁ፡፡

**አመሰግናለሁ!!!**